# የወዘበሬታ!

(ለገሞራው እንጉርጉሮ ከዘነበ በቀለ)

አንበሣው ተኝቶ፣ ቆሞ ነብር  ያለቅሳል፣
አይጥ ተሰብስቦ፣ ይመክራል ይዘክራል፣
ውሻ በግቢው ውስጥ ጩኸቱን ያሰማል፣
ፍየል ደረት ጥላ
በበግ አጀብ ታጥራ፣
ትደቃለች በእጇ፣
ልክ እንደኩያዋ፣ ልክ እንደወዳጇ!

ነብር እሪ! ይላል ስቅስቅ ብሎ እንደሰው፣
ግርማ ሞገስ ጓዱ፣ ስለጠፋ አንበሳው፣
አንገብግቦት በጣም፣ በአይጥ መደፈሩ፣
አስገምጋሚው ድምፁ፣ እርቆት ከምድሩ።

"የጠላን ጎደሎ ጠላን ይሞሉታል፣
የውሀን ጎደሎ ውሃን ይሞሉታል፣
የቀንን ጎደሎ ምን ያደርጉበታል?!"

እንዳለው ከያኒው
ተዘናጋንና፣ ለማዳን ተባብሮ፣
ድንገት በሞት ቢያዝ፣ አንበሳው ተኝቶ፣
ሊቀብር ተሰየመ፣ አይጥ ተጠራርቶ፣
ከት ብላ ሳቀች ጦጢት ከዛፏ ላይ፣
ነገሩን ተረድታ፣ የግድምድም ስታይ፣
የትናንት በትናንት፣ የዛሬን በዛሬ፣
ማሰብ ማለማቸው፣ ለመቀየር ነገን፣ አንቤን በገመሬ።

የድመት እመቤት፣ ከቢሮ ተቀምጣ፣ መካሪ ዘካሪ፣
ድንቄም ሀዘንተኛ አንበሳን ቀባሪ!
ያይጥ ጅራት አማኝ፣ ጎታች ተጠዋሪ፣
ዲስክራሲያቶ ባፋንኩሎ አስካሪ!